# በማህበረሰብ ውስጥ COVID-19 እንዴት ይሰራጫል

ሁሉም COVID-19 ያለባቸው ሰዎች የህመም ስሜት አይሰማቸውም። ምንም እንኳን የህመም ስሜት ባይሰማቸውም፣ ቫይረሱን ለሌሎች ማስተላለፍ ይችላሉ።

አንድ COVID-19 ያለበት ሰው ወደ ሰርግ፣ ወይም ወደ ለቅሶ፣ ወይም ወደ ሌላ ማንኛውም ብዙ ሰዎችየተሰበሰቡበት ቦታ ከሄደ፣ እዚያ ላሉት ሰዎች ቫይረሱን በቀላሉ ሊያስተላልፍ ይችላል። ይህ ደግሞ በይበለጥ እውን የሚሆነው ሰዎች ጭምብሎችን ሳያደርጉ ሲቀሩ፣ እና ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት የማይጠብቁ ሲሆን ነው።

በእነዚህ ዝግጅቶች ላይ በቫይረሱ የተጠቁ ሰዎች ደግሞ ቫይረሱን ወደ ቤተሰቦቻቸው እና ጓደኞቻቸው ይወስዱታል። ከከተማ ውጪ የሚኖሩ ከሆኑ፣ COVID-19 አብሯቸው ይሄዳል።

አብሯቸው የሚኖሩ ሰዎች በሙሉ በቫይረሱ ሊያዙ ይችላሉ። እናም እነዚህ ሰዎች ወደ ስራ፣ ወደ ትምህርት ቤት፣ ወይም ሰው ወደሚሰበሰብበት ማናቸውም ቦታ ከሄዱ፣ እዚያ ያሉ ሰዎችም እንዲሁ ሊያዙ ይችላሉ።

ሰዎች ስርጭቱን ለማቆም እርምጃ ካልወሰዱ በስተቀር በአንድ ሰው ላይ የጀመረው COVID-19 በፍጥነት፣ በአስርታት የሚቆጠሩ፣ ወይም ከዚያም በላይ ሰዎችን ሊይዝ ይችላል።

ቤተሰብዎን፣ ጓደኞችዎን፣ እንዲሁም ያማያቋቸውንም ሰዎች ለመጠበቅ እርምጃ ይወሰዱ።

ብዙ ሰው ከሚሰበሰብባቸው ቦታዎች ይራቁ።

ጭምብል ያድርጉ።

ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ የ6 ጫማ ርቀት ይጠብቁ።

እጆችዎን በተደጋጋሚ ይታጠቡ።

እና ካመምመዎት በቤትዎ ይቆዩ።

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

10/20/20 (Amharic)

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፣ በ651-201-4989 ላይ ይደውሉ።*